# 6

# ማንነት እና አውድ



# 06 ማንነት እና አውድ

## ይዘቶች

**በቡድኖች መካከል የሚደረግ ውይይት ሚና**

**ጥያቄዎች ለቡድን ውይይት**

**የጥላቻ ፒራሚድ**

#DEFYHATENOW | **ምዕራፍ** 6

# ማንነት እና አውድ

## በቡድኖች መካከል የሚደረግ ውይይት ሚና

በተለያዩ ቡድኖች መካከል በተለይ የተለያየ ሃይማኖት እና እምነት ባላቸው ማህበረሰቦች መካከል የሚደረግ ቀጣይነት ያለው እና ውጤታማ ውይይት በቡድኖች መካከል ያሉ ውጥረቶችን ወይም ጥርጣሬ በመቀነስ እንደ ውጤታማ የመከላከያ እርምጃ ሊያገለግል ይችላል።

በቡድን መካከል ትርጉም ያለው ግንኙነት አለመኖር፣ ማግለል እና ለሌሎች ባህል ፍላጎት አለመኖር ብዙውን ጊዜ በቡድን መካከል ለሚከሰቱ አለመግባባቶች እንዲሁም “የጥላቻ ንግግር” በጣም የተስፋፋበት ፣ ዓመፅ ፣ ጠላትነት ፣ ወይም አድልዎ የመፍጠር ዕድሉ የበለጠ ሊሆን ይችላል፡፡

### ይህ በተለይ ሊከሰት የሚችለው

- በቡድኖች መካከል ያሉ ውጥረቶች ወደ አመፅ የተቀየሩበት ታሪክ ካለ፡ ወይም፤
- ትክክለኛ የጥቃት እና አድሎ አጋጣሚዎች።

### ውጤትማ ለመሆን

- ውይይቶች እውነተኛ የአስተሳሰብ ልውውጥ ሊኖራቸው ይገባል።
- ልዩነቶችን እና አለመስማማቶች ላይ ውይይቶችን እንዲደረጉ ማስቻል።
- ውይይቶች አካታች መሆን አለባቸዉ። ማህበረሰብ ከ’ባህላዊ’ መሪዎች ባለፈ እንዲወከሉ መፍቀድ በተለይም የሴቶች ፣ የሴት ልጆች ፣ የወጣቶች እና የተፈናቀሉ/ አነሳ ማህበረሰብ ድምጾችን ወደ ፊትለፊት በማምጣት አካታች ሊሆኑ ይገባል።

ውይይቶች መደበኛ ያልሆኑ ልውውጦችን በማህበረሰቦች መካከል እንዲካሄዱ የሚያስችሉና አካታች መሆን ይገባቸዋል። ለምሳሌ በስፖርት ወይም ባህላዊ ልውውጦችን አውድ ወይም የጋራ የሚያሳሳቡ ተግባራዊ ጉዳዮችን መፍትሄ ለመፈለግ  መተማመንና ትስስርን ለመገንባት ጠቃሚ መሆኑን ማረጋገጥ ይችላል። በቡድኖች መካከል የሚደረግ ውይይት እና ግንኙነት ተነሳሽነቶች ከመንግስት እና ፖሊሲ ከሚቀርፁ እና ሃይማኖታዊ መሪዎች ህዝባዊ ድጋፍን ሲያገኝ ተፅእኖ ማሳደግ ይቻላል፡፡

ከመደበኛ ወይም መደበኛ ያልሆነ “ውይይቶች” አውድ ውጭ ፣ የተለያዩ ማህበረሰቦች ተወካይ ፣ በተለይም የሃይማኖት መሪዎች እና ሌሎች የህብረተሰብ መሪዎች አለመቻቻል እና አድሎአዊነት ላይ እንዲናገሩ ብቁ ማድረግ  ይገባል ፡፡ ይህ በተለይ የአለመቻቻል እና የመድልዎ ደጋፊዎች እራሳቸውን እንደ የተወሰነ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ተወካይ አድርገው ወይም የተወሰኑ ማህበረሰቦችን ወክለው በሚንቀሳቀሱበት ግዜ አስፈላጊ ነዉ፡፡ የሃይማኖት እና የማህበረሰብ መሪዎች እነዚህን የይገባኛል ጥያቄ ለማስተባበል ብቻ ሳይሆን ፣ በግለሰቦቹ አቋም ላይ ለመሳተፍ እና ለመሞገት እንዲሁም አሳማኝ አጸፋዊ ምላሽ ለመስጠት ኃላፊነት አለባቸው።

**ግንዛቤ ስለ ቅድመ - ፍረጃ**

በዓለም ዙሪያ ያሉ ማህበረሰብዎች የተለያዩ ጎሳዎች ፣ ሃይማኖት ወይም ብሄር ቡድኖች ያሏቸው ሀገሮችን ያቀፉ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ቡድኖች አንድ ላይ ለመኖር የማይጣጣሙ ይመስላቸዋል፡፡ ይህም በታሪካዊ ፣ በቅኝ ግዛት ወይም በቅርብ ጊዜ ክስተቶች ምክንያት ሊሆን ይችላል ፡፡ ይህ ግጭት ወደ ሚያስከትል ውጥረት ሊያመራ ይችላል፡፡

ማንነቶች ዉስብስብ እንደሆኑ ሁሉ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችን መፍታት ከባድ ነዉ፡፡ በማህበረሰባችን ዉስጥ የበላይ በሆኑ ቡድኖች ኢላማ ሚደረጉ ማንነቶቻችንን እናዉቃቸዋለን፡፡ ስለሆነም በተወሰነ ደረጃ በማንነት የማንገናኛቸዉ ቡድኖች ላይ ቅደመ-ፍረጃ  ይኖረናል አድልዎም እናደርጋለን፡፡ ማንነቶች የማይለዋወጡ አይደሉም በየቀኑ ምንደራደራቸዉ ነገሮች ናቸዉ፡፡

እንደ አንድ ቡድን አባል ማንነታችን የበላይ ከሆኑ ቡድን አባላት ከሆኑ ግለሰቦች ጋር ባለን መስተጋብር በግለሰብ ደረጃ ማንነታችን ጥያቄ ዉስጥ ሊገባ ይችላል ፣ ልክ እኛ የምንገኝበት ቡድን በሀገር እና አለም አቀፍ ደረጃ አደጋ ሊያጋጥመዉ እንደሚችል፡፡

ስለ ማንነት መማር እና ስለ ቅድመ-ፍረጃዎች ግንዛቤ ሚያስፈልገን ልዩነቶቻችንን እና ግጭቶችን ለመቆጣጠር እንድንችል ነዉ፡፡ የራስዎን ማንነት በመገንዘብ ፣ ይህ ማንነት ለእርስዎ ምን ማለት እንደሆነ መረዳት እና የሌሎችን ማንነት እንዴት መቀበል እንዳለብዎት መማር ግጭትን ለመከላከል እና በተከሰተ ግዜም ለመቆጣጠር ከሚረዱ አስፈላጊ ክፍሎች አንዱ ነዉ፡፡

**ቅድመ - ፍረጃን በተመለከተ አጠቃላይ ግምቶች** (Cotton, 1993)

- ቅደመ-ፍረጃ የተማርነው ነው እንዲሁም ልንተወዉ ምንችለዉ ነገር ነዉ፡፡
- ቅደመ-ፍረጃን ለመፍታት ውጤታማ የሆነው ስነ ዘዴ በራስ ላይ ማተኮር ነው ፣ ከዚያም በቡድኖች መካከል ያሉ መመሳሰሎችን እና ልዩነቶችን መመርመር ነው።
- ስለራሳቸው ጥሩ ስሜት ያላቸው ሰዎች ሌሎችን ማዋረድ/ስም ማጥፋት አያስፈልጋቸውም።
- እውነታዎች ብቻ ወደ የተሻሉ የቡድን ግንኙነቶች አይወስዱም። ይህ የትብብር ትምህርትና ጥልቅ አስተሳሰብ ላይ ያተኮረ ትምህርትን ይፈልጋል።

**?**

## ሊታሰብባቸው ሚገቡ ጥያቄዎች

እኔ ማን ነኝ?


እራስዎን እንዴት ይለያሉ?

እኛ ማን ነን?

- ባህላዊ አመጣጠን እና አስተዳደጎን እንዴት ይገልፁታል?
- እራሶን እንዴት ይለያሉ/ይገልፃሉ (እድሜ ፣ ጎሳ ፣ ዘር ፣ ፖለቲካ ፣ ሃይማኖት ፣ ጾታ)?
- ለቤተሰቦ እና ለማህበረሰብ ቡድኖ ከፍተኛ ቦታ የነበራቸው እሴቶች እና ባህሎች ምን ነበሩ?
- እራስን ከአንድ የተወሰነ ቡድን አባል ማድረግ ምን ጥቅሞች እና ተግዳሮቶች አሉት?
- ከአካባቢ ፣ ከሁኔታዎች እና ልምዶች ጋር በተይያዘ የማንነቶን ዋና ዋና ገፅታዎች ይመርምሩ።
- የማንነት ድርርቦች ፡ ሰፊ እይታ ከግል እይታ ጋር ሲነፃፀር።
- የጋራ/ጎሳ/የፖለቲካ/የሃይማኖት/የሞያዊ ማንነት - በተለያዩ መስመሮች እየደበዘዙ ሄደዋል።

# የጥላቻ ፒራሚድ

ፒራሚድ ከታች ወደ ላይ ውስብስብነቱ እያደገ የሚሄድ አድሎአዊ ባህሪዎችን ያሳያል። ምንም እንኳን በየደረጃው ያሉ ባህሪዎች ግለሰቦችን እና ቡድኖችን በአሉታዊ ሁኔታ ተፅእኖ የሚያደርጉ ቢሆኑም አንድ ሰው ፒራሚዱ ወደ ላይ ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር ባህሪያቱ በይበልጥ አስጊ የሆኑ መዘዞች አሉት። እንደ ፒራሚድ  የከፍተኛው ደረጃዎች ከዝቅተኛ ደረጃዎች ድጋፍ ያሚያገኙ ናቸው። ሰዎች ወይም ተቋማት በዝቅተኛ ደረጃዎች ላይ ያሉትን ባህሪያትን ተቀባይነት ሲኖራቸው ወይም “መደበኛ” አድርገው የሚቆጥሩ ከሆነ በሚቀጥለው ደረጃ ያሉ ባህሪዎች የበለጠ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል። ለዘር ማጥፋት ጥላቻ ከየት እንደመጣ ለሚጠይቁ የዓለም ማህበረሰብ ምላሽ ለመስጠት፤ የጥላቻ ፒራሚድ የዘር ማጥፋት ጥላቻ የተገነባው በፒራሚድ ዝቅተኛ ደረጃዎች ውስጥ የተገለፁ ባህሪዎችን በመቀበል መሆኑን ያሳያል።




የጥላቻ ንግግር ፒራሚድ

ምንጭ፡ CARD (የመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል ) የፀረ-ጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃዎች መመሪያ